# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

## የ1ኛ ሩብ ዓመት ዜና መጽሄት



መስከረም / 2018 ዓ.ም

ዋና አዘጋጆች፡-
ወንድወሰን አካሌ
ፍቅር ሰጡቴ

ሌይአውትና ዲዛይን፡-
ፍቅረግርያም ይትባረክ

https://t.me/AAFarmersandUrbanAgriculture

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

@VoiceofAddisUrbanAgri

Farmeragr2020@Gmail.com

http://www.aafuadc.gov.et/

# ማውጫ


የተቋሙ ራዕይ፣ተልዕኮ እና እሴቶች ---------------------------------------------------1

የኮሚሽኑ ስልጣን፣ ተግባራትና ኃላፊነት ---------------------------------------------2

ስለከተማ ግብርና ግንዛቤ ------------------------------------------------------------3

እጽዋትን ኳራንታይን ከማድረግ አንጻር ---------------------------------------------5

የሰንበት ገበያ ከፊል ገጽታ -------------------------------------------------------------6

እውቅናና ሽልማት ሰልማት ገጽታ --------------------------------------------------------7

ግብርና ከማምረትም በላይ ነው ---------------------------------------------------------9

በመዲናዋ ከሚከናወን ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ አንጻር -----------------------------------12

ከተቋማዊ ሪፎርም የአገልግሎት አንጻር --------------------------------------------14

# የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

## ስለከተማ ግብርና ምን ያህል ያውቃሉ?

የከተማ ግብርና ልማትን በማስፋፋት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ በመፈናቀላቸዉ ተጎጂ የሆኑ አርሶ አደሮችን እና ቤተሰቦቻቸዉን ከደረሰባቸዉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ችግሮች ማላቀቅ እና በዘላቂነት ማቋቋም እንዲሁም የእንስሳት ጤና አገልግሎትን እና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የኢንስፔክሽንና ሬጉላሪ አሰራርን በማሻሻል የህብረተሰቡን የበሽታ ተጋላጭነት መቀነስ እና አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ትኩረት ሰጥቶ የሚያከናውናቸው ተግባራት ናቸው። ሁሉን አሳታፊ የሆነ የከተማ ግብርና ተጠቃሚነት እንዲፈጠር ደግሞ አግባብነት ያለው የኮሙዩኒኬሽን ተግባቦትን መጠቀም መተኪያ የሌለው ጉዳይ ነው።

የከተማ ግብርና ማለት አነስተኛ በሆኑ ቦታዎች ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የእንስሳት (የዶሮ፣ወተት፣ማር፣ና ድለባ) የእፅዋት (አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት) ልማት በማካሄድ ማምረትና የተመረቱ ምርቶችን ማቀነባበር፣ በማከፋፈል ጨምሮ ምርቱን ለቤት ፍጆታ ከማዋል ጥቸገር ለሽያጭ በማዋል ተጨማሪ የገቢ ምንጭ  እንዲፈጥር ያደርጋል።

ኮሚሽኑ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከግብ ለማድረስ እየሰራ ሲሆን እነርሱም የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ማቋቋም እና በቀጣይም አርሶ አደሩ ከከተማዋ ልማት ጋር አብሮ እንዲለማ ማድረግ፣ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በከተማው የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ለከተማዋ የሚቀርቡ የግብርና ምርትና ግብዓት ጥራት እና ሃይጅን ተጠብቆ መቅረቡን ማረጋገጥ ነው። ከዚህ የተነሳ የኮሚሽኑ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬትም እነዚህን መሰረታዊ አጀንዳዎች ለማሳካት የመረጃ ጥራትና ተደራሽነት ማስፋት እና የተቀናጀ የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ሥርዓትን ማሻሻል በዋናነት ትኩረት በማድረግ እየሰራ ይገኛል።

በመሆኑም የኮሚሽኑን መደበኛ ስራዎች እና ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታውን የዋጀ በተለያዩ የኮሙዩኒኬሽን አግባቦች ወቅቱን ጠብቆ ተዓማኒ የሆኑ መረጃዎችን ተደራሽ የማድረግ ስራ ይሰራል።

የከተማ ግብርና ጥቅም  ለህብረተሰቡ  በአነስተኛ ወጪ ትኩስ ጤናማና የተመጣጠነ የአትክልት ምግቦችን እንዲመገብ ያስችላል፤በዚህም ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ እንዲፈጠር ያደርጋል፤የሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዲያደጉና በራስ መተማመን እንዲጎለብት ያደርጋል፤ለሴቶች፣ ወጣቶችና አረጋውያን የስራ

እድል እንዲፈጠር ያረጋል።የመኖሪያ ግቢን እንዲሁም የአካባቢ ውብትን በመጠበቅ ሰዎች የእለት ተእለት ስራቸውን እና ውሎዎቻቸውን በተነቃቃ መንፈስ እንዲያሳልፉ ያስችላል።የአረንጓዴ ሽፋንን ከፍ በማድረግ በከተማ የሚስተዋለውን ከፍተኛ የሙቀት መጠን እንዲቀንስ ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል።በከተሞች የስራ እጥነትን ይቀንሳል።በከተሞች የሚፈጠረውን የምግብ እጥረትና የዋጋ ውድነትን የቀንሳል።የቤተሰብ ተጨማሪ የገቢ ምንጭን በማሳደግ የተሻለ ኑሮ እንዲኖራቸው ይረዳል።

# የተቋመ ራዕይ፣ተልዕኮ እና እሴቶች

## የተቋሙ ራዕይ /Vision/



በ2022 አዲስ አበባ የከተማ ግብርና የተስፋፋባትና የአርሶ አደሩ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የተረጋገጠባት ከአፍሪካ ከተሞች በከተማ ግብርና ተምሳሌት ሆና

## የተቋሙ ተልዕኮ /Mission/



ህብረተሰቡን በከተማ ግብርና በስፋት በማሳተፍ ለከተማ የሚስማማ የኤክስቴንሽን ስርዓት ሥራ ላይ በማዋል፣ ጤናማ የሆነ የግብርና ምርት አቅርቦት በማሳደግ፤ በልማት ምክንያት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮችን በዘላቂነት በማቋቋም እንዲሁም ከችግር ተጋላጭነትን በመከላከል ከከተማው ዕድገት ጋር አብረው እንዲለሙ በማድረግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

## የተቋሙ የአሰራር መርሆዎችና እሴቶች /



- ምግባችን ከደጃችን፤
- ፍትሃዊነት፤
- አገልጋይነት፤
- አሳታፊነትና አካታችነት፤
- ለላቀ ለውጥ ዝግጁነት
- ትኩረት ለአካባቢ ደህንነት፤

## የኮሚሽኑ ስልጣን፣ ተግባራትና ኃላፊነት

1.የከተማ የግብርና ምርት በጥራት የሚመረትበት፣ ለገበያ የሚቀርብበትን እና የግብርና ልማት የሚገለፀበትበት ስልት ይቀይሳል፣ ያስፈጽማል፣

2.ነዋሪዎች በከተማ ግብርና እንዲሳተፉ ያበረታታል፣ በተለያዩ የግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት ምርትና ምርታማነታቸዉ እንዲጨምር ዘመናዊ የግብርና ግብዓት እንዲቀርብላቸው ሙያዊ ድጋፍና ምክር እንያገኙ ያደርጋል፣

3.የእንስሳት በሽታዎች ስርጭትን ያጠናል፣ ለበሽታ ስርጭት የተነሳ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ለመንግስትና ለአርቢዎች ያሳውቃል፣ ለእንስሳት አርቢዎች የእንስሳት ህክምናና የክትባት አገልግሎት ይሰጣል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል፣ የዕብድ ውሻ በሽታ መከላከያ ክትባት ይሰጣል፣ ታክመው መዳን የማይችሉ እና ባለቤት የሌላቸውን እንስሳት ያስወግዳል፣

4.ለእንስሳት አርቢዎች የማዳቀል አገልግሎት ይሰጣል፣ የተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ዉጤቶች፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ለአርሶ አደር እንዲዳረስ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውንም ይከታተላል፣ ለአርሶ አደሮች ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፣

5.የእንስሳት እና የዕጽዋት ማራቢያና ማባዣ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣

6.የእንስሳትና የእጽዋት የኳራንቲን አገልግሎት ይሰጣል፣ በከተማው ውስጥ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና የአገልግሎት ዘመናቸው ያላለቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ መድሃኒቶችን ለሚያስወግድ አካል ያሳውቃል ፣

7.በመዋቅራዊ ፕላኑ ለእንስሳት፣ ለሰብል፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ገበያዎችና ለከተማ ግብርና የተከለሉ ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት እንዲዘጋጁና በዘመናዊ መንገድ እንዲለሙ ያደርጋል፣

8.በግል የሚቋቋሙትን የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች፣ ላቦራቶሪዎች፣ የቀዳና ሌጦ መጋዘኖች፣ ጸረ-ተባይ ማከማቻ መጋዘኖችና መሸጫ መደብሮች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ደረጃና ጥራት ጠብቀው መስራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

9.በህግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት፣ በማህበራት እና በግል ቄራ ድርጅቶች የእርድ እንስሳትና የሥጋ ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ሕገወጥ የእንስሳት እርድና በሕገወጥ መንገድ የታረደ ስጋ ዝውውርን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል

ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

10.ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮች ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላት ጋር በመቀናጀት የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የመኖሪያ ቤቱ እስኪዘጋጅ ድረስ የቤት ኪራይ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

11.በልማት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተነሱ ተነሺ አርሶ አደሮችን ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እደል ፈጠራ ፕሮግራሞች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤ በተሰጣቸው የክህሎት ሥልጠና መሠረት በአካባቢው በሚፈጠሩ የሥራ ዕደሎች ቅደሚያ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይከታተላል፤

12.የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን የኑሮ ሁኔታ በዘላቂነት ለማሻሻል የሚያስችሉ አዳዲስ ኘሮጀክቶችን ይቀርፃል፤ ለፕሮጀክቱ የሚያገለግሉ የማምረቻ እና የመሸጫ ማእከላትን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

13.ኑሯቸዉ በግብርና ስራ ላይ የተመሠረተ አርሶ አደሮች የያዙት መሬት መጠን ልኬት እንዲወሰድና የባለይዞታነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሰጣቸዉ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል ፤

14.አርሶ አደሮች ባላቸው ይዞታ ላይ በግላቸው፣ ከአርሶ አደር ጋር በመደራጀት ወይም ከባለሀብት ጋር በመጣመር እንዲያለሙ አሰራር ይዘረጋል፣ ያስተባብራል፣ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

15.ምንም ገቢ የሌላቸዉና መስራት የማይችሉ አርሶ አደሮች ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማህበራዊና የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

16.ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮች የተሰጣቸውን ካሳ አቀናጅተው ወደ ተሻለ ልማትና የኢንቨስትመንት አማራጮች የሚሰማሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

17.ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ የልማት ተነሽዎችን መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

18.የተሻለ ልምደና ሀብት ያላቸዉ ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦችን በመለየት አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ በግል ይዞታቸው ወይም ተደራጅተዉ የሚሰማሩበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግበራዊ ያደርጋል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

19.በልማት ይዞታቸውን የሚለቁ ባለይዞታዎች ከመልቀቃቸው በፊት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የይዞታ ማስለቀቅ ሂደት መተግበሩን ይከታተላል፤

20.በልማት ስራዎች እና መልሶ ማልማት ተነሽ ለሆኑ አርሶ አደሮች ተገቢውን የካሳ ግምት መተመኑን፣ የካሳ ክፍያ መፈጸሙን፣ ምትክ ቦታ መዘጋጀቱን፣ መሸንሸኑን፣ የምትክ ቤት ማግኘታቸውንና መቀበያ ሰርተፊኬት መሰጠቱን ይከታተላል፤

# ስለከተማ ግብርና ምን ያህል ያውቃሉ

የከተማ ግብርና ማለት አነስተኛ በሆኑ ቦታዎች ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የእንስሳት (የዶሮ፣ወተት፣ዓሣና ድለባ) የእፀዋት (አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት) ልማት በማካሄድ ማምረትና የተመረቱ ምርቶችን ማቀነባበር፣ በማከፋፈል ጨምር ምርቱን ለቤት ፍጆታ ከማዋል ባሻገር ለሽያጭ በማዋል ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በመፍጠር ነው።

የግብርና ምርትና ምርታማነት በመጠንና በጥራት በማሳደግ ኢኮኖሚን በማሻሻል በከተማና በከተማ ዙሪያ የሚኖረውን ህብረተሰብ የስርዓተ-ምግብና የምግብ ዋስትና እንዲሻሻል የሚያደርግ ማለት ነው፡
፡


















# ስለከተማ ግብርና ምን ያህል ያውቃሉ

የእጽዋት ኳራንታይን አንዱ እጽዋትና የእጽዋት ውጤቶች ለተጨማሪ ኢንስፔክሽን ወይም ለማከም ኦፊሴላዊ በሆነ መንገድ ለተወሰነ ጊዜ ማገለል ወይም ዘርንና እጽዋትን ከሚጎዱ ሕይወት ያላቸው ተባዮች ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር እንዳይገባ ለመከላከል የሚደረግ የቁጥጥር ተግባር ነው። ቁጥጥሩ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ፣ ወደ ውጭ አገር በሚላኩ እና በአገር ውስጥ በሚዘዋወሩ እጽዋት፣ የእጽዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር በሚደረግባቸው ቁሳቁሶች ላይ ይካሄዳል።

ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ገቢ ምርቶችን ስንመለከት በአዳማ የእጽዋት ኳራንታይን ጣቢያ በዋናነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡት የአፈር ማዳበሪያ እና የእርሻ ኬሚካሎችን ሲሆኑ እነዚህን በብዛት የምናመጣባቸው አገሮችም ቻይና፣ ሆላንድ፣ ሕንድ፣ ኖርዌይና ጀርመን ናቸው። እነዚህ ሲገቡ የሚያመጡት ሰነድ ላይ አስፈላጊ ነገሮች መሟላታቸውን ካረጋገጥን በኋላ ጉሙሩክ ጣቢያ በመገኘት በሰነዱ መሰረት መሆናቸውን አካላዊ ምልከታ በማድረግ ሕጉን ጠብቆ የገባ መሆኑን ስናረጋግጥ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መልቀቂያ እንሰጣለን። ሌላኛው የኳራንታይን ጣቢያው የሚሠራው ሥራ ለአመጭና ላኪዎች ንግድ ፍቃድ አውጥተው በዘርፉ ላይ ከመሰማራታቸው በፊት በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተቀመጡ መሥፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው እንጽፋለን። ባለሥልጣን መ/ቤቱም ለንግድ ሚ/ር ንግድ ፍቃድ እንዲሰጣቸውና ንግድ ፍቃድ አውጥተው በዘርፉ እንዲሰማሩ ደብዳቤ ይጽፋል ማለት ነው።

በኳራንታይን ጣቢያው 4ኛው ሥራችን የሕክምና አገልግሎት ሲሆን በዚህ ዘርፍ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ እህሎች በአገባቡ ታክመው 72 ሰዓት ታሽገው ከተባይ ነጻ ሆነው እንዲሄዱ የምናደርግበት የአሰራር ሥርዓት ነው። በአጠቃላይ የአዳማ የእጽዋት ኳራንታይን ጣቢያ እነዚህ ከላይ የተገለጸውንና ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።





## አሁድ ገበያ ለዋጋ መረጋጋት ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ነው፡፡

### የሰንበት ገበያ ከፈል ገጽታ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቅዳሜና እሁድ ገበያ የነዋሪዉን የኑሮ ጫና እያቃለለ ይገኛል፡፡ስለሆነም በከተማው የተለያ መዳረሻዎች የሚገኙ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች በስራ አቅርቦት ሸማችን በቀጥታ ከአምራች እያገናኙ በመሆኑ የዋጋ ንረት እንዳይፈጠር ከማድረግ አንፃር የላቀ ሚናቸዉን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የእሁድ ገበያ መዳረሻዎችም ሸማቾችን እያስተናገዱ የሚገኙ ሲሆን ነዋሪዎች በእሁድ ገበያዎች ተገኝተዉ በመገበያየታቸዉ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እያገኙ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

















## አውቅናና ሽልማት ለልማት እና ለበለጠ ውጤት ትልቅ አቅም ነው።

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ከማዕከል እስከ ወረዳ ላለው መዋቅር እውቅናና ሽልማት ሰጥቷል።

ኮሚሽኑ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀምን መነሻ አድርጎ ከ11ዱም ወረዳዎች 1ኛ ለወጡ 11 ወረዳዎች፣ ከማስፋፊያ እና ከማህል ክፍለ ከተሞች መካከል 1ኛ ለወጡ ሁለት ክፍለ ከተሞች በድምሩ ለ13 ተቋማት የሞተር ሳይክል ሽልማት አበርክቷል።

ሁለተኛ ለወጡ 11 ወረዳዎች እና ሁለት ክፍለ ከተሞች በድምሩ 13 ላፕቶፖች እና የሦስተኛ ደረጃ ለያዙ ከወረዳና ከክፍለ ከተሞች ደግሞ ፕሪንተር እና ዋንጫዎችን በሽልማት አበርክቷል።

በሌላ በኩል ኮሚሽኑ ለማዕከላት፣ ለዳይሬክተሬቶች፣ ለቡድኖች እና ለፈፃሚዎች ቀደም ካለው ጊዜ በተለየ መልኩ አበረታች የሆኑ ሽልማቶችን ሰጥቷል።

የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ የተሰጡ ሽልማቶች ለመጭው የ2018 በጀት ዓመት ሥራችን አቅም ናቸው ብለዋል።

አያይዘውም በሰለቱ የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድን በጋራ ማየታችን እና የ2017 በጀት ዓመት እውቅናና ሽልማት ማካሄዳችን ጥንካሬዎቻችንን አጠናክረን ለማስቀጠል እና ክፍተቶቻችንን የዕቅዳችን አካል አድርጎ ለመሄድ ያግዛል ብለዋል።

እውቅናና ሽልማት የተሰጡ ተቋማትም የዘንድሮው ከመቸውም የተለየና ደስታን የፈጠረልን ነው ብለዋል። እውቅናና ሽልማትም በዚህ ልክ መሰጠቱ ለስራችን ትልቅ መነሳሳትን ይፈጥራል ብለዋል።

ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ የተሰጠው ሽልማት ለተቋማትና ለግለሰቦች ሲሆን ሁሉም በነበራቸው የበጀት ዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም ምዘና መሰረት መሆኑን እንስተው ይህ በቀጣይ ለሁሉም አመራርና ሰራተኞች ትልቅ መነሳሳትን እንደሚፈጥር ተናግረዋል።












2017



## ግብርና ከማምረትም በላይ ነው!፡፡

ሀገራችን ለግብርና ልማት የተሰጠች ሀገር ናት። ለዘርፉ ውጤታማነት ተስማሚ የአየር ንብረት፣ በቂ የገጸ ምድርና የከርሰምድር ውሃ፣ ለም መሬትና አምራች የሰው ሃል ያላት አገር መሆኗ አያከራክርም።

ከተማችን አዲስ አበባ ደግሞ ለከተማ ግብርና ሥራ እጅግ በጣም ምቹና ሊያሰራ የሚችል ገፀ-በረከት ያላት ናት፡፡ ዙሪያዋ በአርሶ አደሮች የታጠረች፣ ኗሪዋ ለግብርና ሥራ አዲስ ያልሆነ፣ ለዘመናዊ ግብዓትና ቴክኖሎጂ እጅግ በጣም ቅርብ የሆነች ናት፡፡

በመሆኑም የሀገራችን ብሎም የከተማችን ዜጎች የህልውና መሠረት የሆነው የግብርና ዘርፍ "ከማምረትም በላይ ነው" ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ስለሆነም የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ የሀሉም አካል የሞት የሽረት ጉዳይ መሆኑን ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም። የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ጉዳይ በግብርናው ምርታማነት ላይ የተመሰረተ ነው። ሌላው የኢንዱስትሪው እድገትም ቢሆን የሚወሰነው በግብርናው ምርታማነት ልክ ነው።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እሳሳቢ እየሆነ የመጣው የኑሮው ውድነት ከዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ ጋር ሊመጣጠን የሚችለው የዘርፉን ምርታማነት በተፈለገው ደረጃ ማሳደግ ሲቻል ብቻ መሆኑን መረዳት ይገባል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የዘርፉን ምርታማነት ማሳደግ የሚያስችሉ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አቅርቦትና በዘርፉ የተሰማሩ የግብርና ቤተሰብ በእውቀትና በአሰራር ብቁ እንዲሆኑ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

የከተማዋን ነዋሪ የግብርና ቤተሰብ ታሳቢ ያደረጉ ምርትን በእጥፍ የሚጨምሩ፣ የአርሶ አደሩንም ጊዜና ጉልበት የሚቀጥቡ የተለያዩ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ተጠናክሮ ቀጥሏል።

የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም ሀተጨማሪ በሌማት ትሩፋትና በመደበኛው የግብርና ሥራ የግብርናውን ቤተሰብ አቅም የመገንባት፣ ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ ልምድና ተሞክሮዎችን የማስፋት ሥራ በስፋት እየተሰራ ይገኛል፡፡



ግብርና ከማምረትም በላይ ነው!፡፡



በመዲናዋ የሚከናወን ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ ለህብረተሰቡ ከፍተኛ የጤና ስጋት ነው።

አዲስ አበባ፣ ነሐሴ 29 ቀን 2017 ዓ.ም

ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ ከጤና ስጋትነቱ በተጨማሪ ከተማ አስተዳደሩን በየዓመቱ ከፍተኛ ገቢ ያሳጣዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፣ የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት፣ የደንብ ማስከበር ባለስልጣን እና ንግድ ቢሮ ከማዕከል እስከ ወረዳ ያለውን መዋቅራቸውን በመያዝ መጭውን አዲስ ዓመትና ሌሎች ብሔራዊ በዓላትን ታሳቢ ባደረገ ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና ሥጋ ዝውውርን ለመከላከል የሚያስችል ውይይት አድርገዋል።

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ፣ ሥጋ ዝውውር እና የእንስሳት ዝውውርን መከላከል ለከተማዋ ነዋሪ የሚቀርበውን የሥጋ ምርት ጥራት፣ ኃይጅንና ደህንነት ማስጠበቅ በመሆኑ ተቋማት ተቀናጅተን በከፋተኛ ኃላፊነት መስራት አለብን ብለወዋል።

የአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና ዝውውር የሚፈፀመው በአብዛኛው ድብቅ በሆኑ ቦታዎች ስለሚሆን በቅንጅት በጥንቃቄ መስራት እንደሚገባ ገልፀዋል።

የአዲስ አበባ ቄራወች ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ተወካይ ወ/ሮ ሰናይት መጭውን በዓላት ታሳቢ በማድረግ ጤናማነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት እርድ አገልግሎት ለመስጠት ድርጅቱ በልዩ ሁኔታ ዝግጅት ማደረጉን አስታውቋል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች የእንስሳት ህገ-ወጥ እርድ እና ዝውውር እንደሚፈጸም ተናግራዋል።

አያይዘውም ህገ-ወጥ እርድ በወንዞች አካባቢ፣ በሆቴሎች ጀርባና በተለያዩ ቅሻሻ ቦታዎች እንዲሁም ከከተማዋ ውጭ ስለሚከናወን ጥብቅ ቅንጅታዊ ሥራ ይፈልጋል ብለዋል።

ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ ከእንስሳት ወደ ሰው ተላላፊ ለሆኑ በሽታዎች ከማጋለጥ በተጨመሪ ሥጋው ስለሚመረዝ የጤና ስጋትነቱ በእጅጉ የከፋ መሆኑን ገልፀዋል።

በውይይቱ ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ በሚያከናውኑ አካላት ላይ ህጋዊ የገንዘብ ቅጣት እንዲሁም የተፈጠረው ህገ-ወጥነት የከፋ ሆኖ ሲገኝ የእስር ቅጣት እንደሚያስከትል ተገልጿል።

በመሆኑም ህብረተሰቡ በየትኛውም ቦታ ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድን ሲመለከት ጥቆማ በመስጠት መተባበር ያለበት መሆኑ ተነስቷል።

ም/ኮሚሽየር ፀጋ ለማ (ዶ/ር) ከሥጋ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ስታንዳርድ ማስጠበቅ እና ከእርድ ቦታ የማስተካከል ሥራ ጋር በተያያዘም ኮሚሽኑ ቀድሞ ሰፊ ስራ መስራቱንና ለሚመለከታቸው አካላትም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መስራቱን ተናግረዋል።

ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና ሥጋ ዝውውር እጅግ አደገኛ ህገ-ወጥ ተግባር ከመሆኑም በላይ ማህበረሰቡን ለከፍተኛ የጤና ችግር ተጋላጭ ስለሚያደርግ ሁላችንም በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት መስራት አለብን ብለዋል።

# ግብርና ከማምረትም በላይ ነው!።

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የከተማ ግብርና ምርት እጥረት እንዳይከሰት በትጋት እየሰራ ይገኛል።

አርቢዎችን በመደገፍ እና የግሉን ማህበረሰብም በማበረታታት የግብርና ምርት በበቂ ሁኔታ ለተጠቃሚው በሰንበት ገበያዎች እና በባዛር ገበያዎች እየቀረበ ይገኛል።

የኮሚሽኑ ተጠሪ ተቋም የሆነው የእንስሳት ልማት እና ልህቀት ማዕከልም መጭውን የአዲስ ዓመት በዓል በተመለከተ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእንቁላል ምርት እና የደለበ ሰንጋ አዘጋጅቶ ለገበያ እያቀረበ ይገኛል።

በከተማችን አዲስ አበባ ከተማ ግብርና ላይ በተሰራው ሰፊ የልማት ትሩፋት የንቅናቄ ሥራ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሆነው ተሳታፊና ተጠቃሚ ደግሞ የራሱን የቤተሰብ ፍጆታ በመሸፈን ለከተማዋ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

በቤተሰብ ፍጆታ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑት የግብርና ቤተሰቦች ከራስ ፍጆታ አልፈው ምርታቸውን ለገበያ እያቀረቡ ያሉ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ነው።

ከ2,000 በላይ የሚሆኑ የመንግስት እና የግል ተቋማትም አብዛኛቹ ግብርና ምርት ማዕከል እየሆኑ ያሉ በመሆናቸው የሰራተኞቻቸውን ፍጆታ እየሸፈኑ ይገኛሉ፣ አንዳንዶቹም ከሰራተኞቻቸው ፍጆታ አልፈው ምርታቸውን ለገበያ እስከ ማቅረብ ደርሰዋል።

ከተማ ግብርና ላይ እየታየ ያለው ሰፊ የግብርና ቤተሰብ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ገበያ ላይ ለሚቀርበው የግብርና ምርት መጨመር እና ለዋጋ መረጋጋት ሚናው የማይተካ ነው።



# ህገ-ወጥነትን መከላከል የጋራ ተግባራችን መሆን አለበት፡፡ ፀጋ ለማ (ዶ/ር)

በማዕከል ደረጃ የተቋቋመው የህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና ሥጋ ዝውውር ቁጥጥር ግብረ-ኃይል በክፍለ ከተማ ደረጃ ለተቋቋመው ተመሳሳይ ግብረ-ኃይል ሲሰጥ የነበረው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ግምገማ አደረገ።

በማዕከል ደረጃ ከአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፣ ከንግድ ቢሮ፣ ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን እና ከአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት የተውጣጣ የህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና ሥጋ ዝውውር እንዲሁም የቁም እንስሳት ዝውውር ቁጥጥር ግብረ-ኃይል በክፍለ ከተማ ደረጃ ለተቋቋመው ተመሳሳይ ግብረ-ኃይል በህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ፣ ሥጋ እና የቁም እንስሳት ዝውውር ዙሪያ ባለፉት ቀናት ሲሰጥ የነበረውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ግምገማ ተደርጓል። የግብረ-ኃይሉ ዐብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና በአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የሰርተፊኬሽን፣ ኢንስፔክሽን፣ ኳረንቲንና ሬጉላቶሪ ዘርፍ ኃላፊ ፀጋ ለማ (ዶ/ር) በመድረኩ ላይ ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና ሥጋ ዝውውር እንዲሁም የቁም እንስሳት ዝውውርን በዘላቂነት መቆጣጠር የሚቻለው እስከ ወረዳ ድረስ ላለው ተቆጣጣሪ ተቋማትና አካላት በጋራ በቅንጅት ሲሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አያይዘውም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራው እስከ ወረዳ ድረስ ላሉ መዋቅሮች እና ለህብረተሰቡ ጭምር የሚሰጥ ይሆናል ብለዋል።

ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ እና ሥጋ ዝውውር ህብረተሰቡን ለጤና ችግር ሊዳርግ የሚችል፣ ፍትኃዊ ያልሆነ የንግድ ውድድር የሚፈጥር፣ እንደ ቆዳና ሌጦ ያሉ ተረፈ-ምርቶች ዓግባቡ ተይዘው ለኢንዱስትሪ ግብዓት እንዳይውሉና እንዲባክኑ የሚያደርግ፣ ለአካባቢ ብክለት መንስዔ የሚሆን በመሆኑ ሁሉም በጋራ ሊታገለው የሚገባ ተግባር መሆኑን ተናግረዋል፡፡እከለውም የተጀመረው የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የቁጥጥር ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።













## በርካታ ቁጥር ያላቸው እንቁላሎች ለአካባቢው ማህበረሰብ ተሰራጩ።

በእንስሳት ልማት እና ልኅቀት ማዕከል ባለፉት ሶስት ቀናት ብቻ በማዕከሉ ባሉት የእንቁላል መሸጫ ሱቆች በርካታ ቁጥር ያላቸው እንቁላሎች ምርት ለአካባቢው ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ተሰራጭቷል።

በማዕከሉ የግብይት ልማት ቡድን መሪ የሆኑት ወ/ሮ ሣራ ንጉሴ እንደገለፁት በየቀኑ በማዕከሉ ባሉት አስራ አንድ የእንቁላል መሸጫ ሱቆች በአስራ አንድ አምራች ማህበራት የተመረተ እንቁላል ለማህበረሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ የተሠራጨ ሲሆን ህብረተሰቡ በፍትሃዊነት እንዲጠቀም የግብይት ስርዓቱን ለመቆጣጠር ማዕከሉ ጠንክሮ መስራት መቀጠሉን አንስተዋል።







**ከሸማችነት ወደ አምራችነት!!!**

# ተቋማዊ ሪፎርም ማከናወን የአገልግሎት አሰጣጡን ያሳልጣል።

የኮሚሽኑ የ2018 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለጀነራል ካውንስል አባላት ቀርቦ ተገመገመ።

ኮሚሽኑ በዝግጅት ምዕራፍ ተቋማዊ ሪፎርም በማከናወን የአገልግሎት አሰጣጡን በማሳለጥ የተጀመረውን ለውጥ ዘላቂ ደረጃ በማስቀጠል ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ አበረታች ተግባራት መከናወናቸው በሰነዱ ተንስቷል።

ከተቋም ግንባታ እና የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ከማሳደግ አንፃር፣የወርቃማ ሰኞ መድረክ ሳይቆራረጥ በመቀጠል የሠራተኛዉን ግንዛቤ እዉቀት ማጠናከር ተችሏል፣የኮሚሽኑ ሰራተኞች ነፃ የምሳ አገልግሎት ማስቀጠል መቻሉ፣የተገልጋዮች ምቹ የማረፊያ ቦታ በየኮሪደር በማዘጋጀት እና የተገልጋይ ቀን ሳይቆራረጥ መቀጠሉ፣ከተቋም ግንባታ አንፃር ከማዕከል እስከወረዳ የሰራተኛ ምጥጥን ስራው ማከናወን መቻሉ፣የሚሰጡ 7 ዋና ዋና አገልግሎቶች ሁሉም በስታንዳርድ መስጠጡ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ተግባር እንደሆነ የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ ተናግረዋል።





የልማት ትሩፋት ንቅናቄ ስራ ማስቀጠል፣ተዓማኒ የሆኑ መረጃዎችን በጥራት አደራጅቶ ከማቅረብ አንፃር ውስንነቶች መኖር፣በከተማ ግብርና ስራ ላይ የተሰማሩትን ወደ ስታንዳርድና ጥራት ማምጣት ላይ፣አብዛኛዎቹ ካፒታል ፕሮጀክቶች ወደ ተግባር እንቅስቃሴ ማስገባት ጋር የተያያዙ እና መሰል ሀሳቦች በውይይቱ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው።



## ምርትና ምርታማነት ሁሉን አቀፍ አሳታፊ አሰራር በመዘርጋት የሚመጣ ውጤት ነው፡፡

የተቋም አመራርና ሰራተኞች፣ ቅንጅታዊ ተቋማት፣ ባለድርሻ አካላት፣ ሲቪክ ማህበራት እና ሌሎችም ያገባኛል ባይ ግለሰቦች ንቀ ተሳትፎ እንደ ተቋም ላስቀመጠው ራዕይ መሳካት ሚናቸው የማይተካ ነው፡፡

ቻይና ኤድ (China Aid) የተሰኘ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በከተማ ግብርና ሰርቶ ማሳያና ግብዓት ብዜት ማዕከል ውስጥ የከተማ ግብርና ሥራን ማገዝ የሚያስችል በርካታ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል፡፡

በማዕከሉ ውስጥ እየሰራ ያለው የግብርና ሥራ ከሰርቶ ማሳያነት ባለፈ ለዘር ብዜት እና ለምርትና ምርታማነት ያለው አበርክቶ ከፍተኛ በመሆኑ ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትንም በስፋት ማሳተፍ እንደሚገባ የኮሚሽኑ የጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ጌታሁን አበበ ገልፀዋል፡፡

የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ አቶ አብደታ ደሜ ድርጅቱ የስልጠና አዳራሽ አደሳት፣ የእንጉዳይ ዘር ብዜት ላብራቶሪ እድሳትና ግብዓት ማሟላት፣ የዞን የግሪን ሃውስ ዝግጅት፣ ዶሮ ቤት ግንባታ፣ ሰባት ዓይነት ዝርያ ያለው የበቆሎ ዘር ሰርቶ ማሳያ፣ ሰባት ዓይነት የእንጉዳይ ዘር እና የጓሮ አትክልት ዘር አቅርቦት፣ የትራክተር ጥገና፣ ለሰራተኞች የአቅም ግንባታ እና ጉብኝት በማስዋብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

ማዕከሉ ለልምድና ተሞክሮ እንዲሆም ለተግባር ተኮር ሥልጠና ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ይገኛል፡፡
















በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን